# የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት አመሠራረት እና አሁን ያለበት ሁኔታ

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ውስጥ የሚገኘውና የአስተዳደር ፍ/ቤት በሚል መጠሪያ የሚታወቀው ተቋም አመሠራረቱና አደረጃጀቱ በየዘመናቱ የተለዋወጠና በቀድሞ ሥያሜው " የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት" ከሚባለው የቀደመ ታሪክ ያለው ነው::

የአስተዳደር ፍርድ ቤት አመሠራረትና ዓላማውን በሦስት ደረጃ ክፍል መግለጽ ይቻላል:: በአንድ በኩል ከ1936 ዓ.ም እስከ 1954 ዓ.ም ያለውን ወቅት፣ በሌላ በኩል ከ1955 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም እና ከ1994 ዓ.ም በኋላ አሁን ያለበትን ደረጃ መቃኘት ይቻላል::

## 1. ከ1936 ዓ.ም እስከ 1954 ዓ.ም

የአስተዳደር ፍ/ቤቱ መቼ ተመሠረተ የሚለውን ጥያቄ በእርግጠኝነት ለመመለስ ባይቻልም በቀድሞው ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ከ1936 ዓ.ም በኋላ ከተዘጋጁ ሠነዶች በመነሣት ፍርድ ቤቱ ከ1936 ዓ.ም በፊትም ይሠራ እንደነበር የሚከተሉት ማስረጃዎች ይጠቁማሉ::

የመጀመሪያው ማስረጃ ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ የአስተዳደር ፍ/ቤቱን በምክትል ሚኒስቴርነት ማዕረግ ይመሩ የነበሩት ብላታ ዴሬሳ አመንቴ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለነበሩት ለክቡር ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው "በመንግሥት ሥራ አስተዳደር ምክንያት ለሚነሱ ክርክሮች የቆመ ፍርድ ቤት የዓመት የሥራ መግለጫ በሚል ርዕስ ያቀረቡት የ1938 ዓ.ም ዓመታዊ የሥራ መግለጫ" ነው:: በመግለጫው ፍርድ ቤቱ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ከመቋቋሙ አስቀድሞ በጽሕፈት ሚኒስቴር ተጠባባቂነት እንዲሠራ መብቱ ተሰጥቶት እስከ 1936 ዓ.ም የፍ/ቤቱ መቋቋም ሣይታወጅ ከቆየ በኋላ በጠቅላይ ሚኒስቴር ተጠባባቂነት እንዲሠራ ተፈቅዷል ....... " በማለት የገለፁት ሲታይ ፍ/ቤቱ ከ1936 ዓ.ም በፊት ይንቀሳቀስ እንደነበር የሚያመለክት ነው::

ሁለተኛው ማስረጃ የመንግሥት ሠራኞች አስተዳደር ኮሚሽን 25ኛ ዓመት በዓሉን ባከበረበት ወቅት "..... የ1923 ዓ.ም በወጣው ሕገመንግሥት የአስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሚቋቋም ተጠቅሶ ስለነበር ከ1933 ዓ.ም ወዲህ የአስተዳደር ፍርድ ቤት በጠቅላይ ሚኒስቴር ሥር ተቋቋመ:: ለአስተዳደር ፍ/ቤት በተለይ የወጣ ደንብ

አልነበረም፡፡ የመጀመሪያው የፍ/ቤቱ ኃላፊ ቢትወዳድ ነጋሽ ነበሩ ..... " በማለት የሰፈረው የጽሑፍ ማስረጃ ይገልፃል፡፡ ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ ባለው ጊዜ የፍ/ቤቱ ኃላፊ የነበሩት ቀደም ሲል የተጠቀሱት ብላታ ዴሬሣ አመንቴና ዋና ዳሬክተሩም ብላታ ትርፌ ሹምዬ የሚባሉ እንደሆኑና በተመሣሣይ ጊዜ ቢትወደድ ነጋሽ በአማካሪ ሚኒስቴርነት ማዕረግ ይታወቁ እንደነበር በወቅቱ በተደረጉት መፃፃፎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

አወቃቀሩን በተመለከተ በ1936 ዓ.ም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ተቋቁሞ ቀደም ሲል የጽሕፈት ሚኒስትር እየተባለ በሚታወቀው አካል ለንጉሡ ቀርበው ይወሰኑ የነበሩ ጉዳዮች ሁሉ ከታህሣስ 12 ቀን 1936 ዓ.ም ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት በኩል እንዲቀርቡ የተወሰነ በመሆኑ በተመሣሣይ ጊዜ ውስጥ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ከጽሕፈት ሚኒስቴር የበላይ ተጠባባቂነት ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የበላይ ተጠባባቂነት እንደተዛወረ መገመት ይቻላል፡፡

ስለፍርድ ቤቱ ሥልጣንና ዝርዝር ተግባር በ1923ቱ ሕገመንግሥት ውስጥ ሰፋ ባለ አገላለፅ ከተቀመጠው በተጨማሪ የተደነገገ ነገር ባይኖርም በወቅቱ ከነበሩ ሠነዶች መረዳት የሚቻለው ፍርድ ቤቱ አሁን ያለውን ይዘት የያዘ እንዳልነበረ እና ይልቁንም ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ጨምሮ ይመለከት ነበር፡፡ ለምሳሌ በሁለት የመንግሥት ተቋሞች መካከል የነበረን የቤንዚን ቀረጥ ክርክር፣ ማናቸውም ዓይነት የመንግሥት ሠራተኞች አቤቱታ፣ በንጉሡ ቤተሠብ አባል ላይ የሚቀርብ አቤቱታና በመሬት ይዞታ ላይ የሚቀርብ ክርክርን መጥቀስ ይቻላል፡፡

## 2. ከ1955 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም

በ1955 ዓ.ም የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት በትዕዛዝ ቁጥር 23/54 እና ኋላም በትዕዛዝ ቁጥር 28/55 እንደተሻሻለው ሲቋቋም ቀደም ሲል በንጉሠ ነገሥቱ በኋላም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥር የነበረው የአስተዳደር ፍርድ ቤት ዋነኛ አካሉ ሆኖ ተቋቋመ፡፡ ከዚህ በኋላ የአስተዳደር ፍርድ ቤት በኮሚሽኑ ሥር ያሉትን የልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች የበላይ ባለሥልጣኖች በሠራተኞቻቸው ላይ የሚሠጡትን የዲስኘሊን ውሳኔ ይግባኝ ሲቀርብለት ይግባኞችን መርምሮ የውሳኔ ሐሳቡን ለኮሚሽነር ጉባዔ የሚያቀርብ አካል ሆኖ እንደተዋቀረ የመንግሥት ሠራተኞች ደንብ ቁጥር 1/1955 የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 269 ከአንቀጽ 98 እስከ 103 እና የኮሚሽኑ አቋም ደንብ ቁጥር 270/55 አንቀጽ 5 በፊደል ተራ ሐ/ ላይ ተመልክቷል፡፡

የአስተዳደር ፍ/ቤት ከ1966 ዓ.ም እስከ 1980 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ የፍርድ ቤቱን ሥልጣን የማጥበብና የማስፋፋት ተጽእኖ የነበራቸው መመሪያዎች ወጥተው ከሕግ ውጭ ሲሠራባቸው እንደነበር ከአንድ አንድ ጽሑፎች የተገኙ ማስረጃዎች ይገልፃሉ:: ሜሪት መጽሔት ጥቅምት 1990 ቅጽ 3 ቁጥር 1 ገጽ 12 እና 13፣

## የአስተዳደር ፍ/ቤት ከ1994 ዓ.ም በኋላ

የመንግሥት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን የሥራ ክርክር ይግባኝ አይቶየሚወስን የአስተዳደር ፍ/ቤት ታህሳስ 25 ቀን 1994 በወጣው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 262/94 አንቀጽ 70 መሠረት ተቋቁሟል::

በዚሁ መሠረት የአስተዳደር ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 262/94 አንቀጽ 70 ንዑስ ቁጥር አንድ፣ ንዑስ ቁጥር ሁለት እና ሦስት መሠረት የሚቀርቡለትን የይግባኝ አቤቱታዎች መርምረው ውሣኔ የሚሰጡ ችሎቶች እንዳሉት:: እያንዳንዱ ችሎት በኮሚሽነር የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና ሁለት አባላት እንደሚኖሩት ተደንግጓል::

## በአስተዳደር ፍርድ በት የሚታዩ ጉዳዮች

1. ከህግ ውጭ አገልግሎቱ በመቋረጡ፣
2. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የተወሰነበት በመሆኑ፣
3. ከሕግ ውጭ ደመወዙ ወይም ሌሎች ክፍያች የተያዘበት ወይም የተቆረጠበት በመሆኑ፣
4. በሥራው ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ጋር በተያያዘ መብቱ በመጓደሉ ቅር የተሰኘ የመንግሥት ሠራተኛ የሚያቀርበውን ይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል::

የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ቀደም ካሉት ጊዜያት ለየት የሚያደርገው እንደበፊቱ ይግባኞችን መርምሮ የውሣኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ተቋም ሣይሆን በራሱ ውሣኔ ሰጭ መሆኑ ነው:: ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በውሣኔው ቅር የተሰኘ ወገን በሕግ ትርጉም ላይ ብቻ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ መሆኑና የአስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ አፈፃፀምን በሚመለከት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኩል የሚፈጸም መሆኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ሥልጣንና ተግባሩ በፊት ከነበረው ሰፋ ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው::

የሥነ-ሥርዓት ሕግን በተመለከተ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የሰጠው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 262/94 ማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 77/1994 አዋጅን ተከትሎ የወጣው ደንብ ነው::

## አስተዳደር ፍርድ ቤት ከመደበኛ ፍርድ ቤት የሚለይባቸው ነጥቦች፣

1ኛ/ የአስተዳደር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ.262/94 አንቀጽ 71 እንደተዘረዘረው ከሥራ በመታገድ በከባድ የዲስኘሊን ጥፋት ቅጣት የተወሰነበት የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታ እና የደመወዝ ወይም የሌሎች ክፍያች የተቆረጠበትና በሥራው ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ጋር በተያየዘ የሚቀርብውን ይግባኝ ብቻ መመርምሮ ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑ፣

2ኛ/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የፌዴራል የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 262/94 ማስፈጸሚያ ደንብ ያለው ሲሆን በሥነ ሥርዓት ሕግ አለመታሠሩ፣ ያለምንም ክፍያ እና በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት መልክ ጉዳዬችን የሚወሰን መሆኑ፣

3ኛ/ የተከራካሪ ወገኖች ወጭን በተመለከተ በደንብ ቁጥር 77/94 አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተደነገገው መሠረት ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ ክርክሩ ያስከተለባቸውን ወጪ በየራሳቸው እንደሚችሉ መደንገጉ፣

4ኛ/ ዳኞች የሚሰየሙት በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር መሆኑ ነው::

## የፌዴራል የመንግሥት ሠራተች አዋጅ ቁጥር 262/94 መሻሻል፣

ከዚህ በፊት የነበረው ደንብ ቁ.1/1955ን ያሻሻለውን በአዋጅ ቁጥር 262/94 በሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገ ከ4 ዓመት በኋላ መሻሻል ያስፈለገበት ዋና ምክንያት፣

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ምንም እንኳን ከአዋጅ ቁጥር 262/1994 መውጣት በኋላ ቀደም ካሉት አመታት ሥልጣንና ተግባሩ ሠፋ ባለመልኩ የተቀመጠ ቢሆንም አዋጁ በሥራ ላይ ውሎ በተግባር ሲፈተሽ በተለይ አሻሚነት ያላቸውና እርስበርሳቸው የሚቃረኑ ሐሳቦች ይዞ በመገኘቱ በአሠራር ላይ ክፍተቶች እንዲፈጠር ማድረጉ፣ በሌላም በኩል አዋጁ ጠቅለል ያሉ ሃሳቦችን በመያዙ እና እነዚህ ሃሳቦች ደግሞ አዋጁን ተግባራዊ በሚያደርጉ አካላት ዘንድ የአሠራር ችግር ማስከተሉ::

አዋጁ ከዚህም ሌላ አሁን ካሉት አዳዲስ አስተሳሰቦች አንፃር በአዋጁ ውስጥ ሊከተቱ የሚገባቸውን አዳዲስ ሃሳቦች እንዲይዝ በማስፈለጉ እና በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አዋጁን በሥራ ላይ በመተርጐም ተግባራዊ የሚያደርጉት በአብዛኛው

የሕግ ባለሙያዎች ሣይሆኑ የአስተዳደር ባለሙያዎች በመሆናቸው በሥራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 262/94 የቋንቋ አጠቃቀሙ በአብዛኛው ቴክኒካዊ በመሆኑ ይህ ደግሞ ተጠቃሚውን በትክክል ያላገናዘበ ሆኖ በመገኘቱ የአዋጁን ቋንቋ በተቻለ መጠን ቀላል ለማድረግ እና ቴክኒካዊ ባልሆኑና ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ በማስፈለጉ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት በአዋጁ ላይ የተቀመጡት ሐሳቦች የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ውጤቶች ከሆኑ አዳዲስ አስተሳሰቦች ጋር መጣጣማቸው አዋጁን በሚተረጉመው አካል ዘንድ የተሻሉ አስተሳሰቦችን እንዳይዝ ያደርጋል በሚል መነሻ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ለተገልጋዩ የሚሰጠውን ግልጋሎት ለማቀላጠፍ የሚረዳ የተለያዩ ፎርሞችን ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ፎርሞችዋና ዋናዎቹ የአቤቱታ አዘገጃጀትን የሚመራ ቅጽ ፣ የውሣኔ ግልባጭ ወይም የመዝገብ ግልባጭ መጠየቂያ ፎርም እና የአፈጻጸም መጠየቂያ ፎርሞች ናቸው፡፡ ፎርሞቹም ከዚህ ጽሑፍ ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

# <u>ለአስተዳደር ፍ/ቤት የሚቀርብ የይግባኝ</u>
# <u>አቤቱታ አዘገጃጀትን የሚመራ ቅጽ</u>

.................... ቀን ........... ዓ.ም

**በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ**
**ለአስተዳደር ፍ/ቤት**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

ይግባኝ ባይ .............................
አድራሻ ................................
መልስ ሰጭ .............................

ሀ/ ይግባኙ የቀረበው መልስ ሰጭ ................... ቀን ............. ዓ.ም በቁጥር ......... ያስተላለፈውን ውሣኔ በመቃወም ነው::

ለ/ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለመመልከት በአዋጅ ቁ. 262/94 አንቀጽ 71 መሠረት ሥልጣን

ሐ/ ይግባኙ የተመሰረተው መልስ ሰጭ ................... ቀን ............. ዓ.ም በተጻፈ ሸኚ ደብዳቤ በሰጠኝ .......... ገጽ የዲስኘሊን መዝገብ ግልባጭ ላይ ነው::

1. የመልስ ሰጭ ውሣኔ ባጭሩ
2. የይግባኝ ባይ ቅሬታ
3. ይግባኝ ባይ የምጠይቀው ዳኝነት

ከዚህ በላይ የገለጽኩት እውነት መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሠረት አረጋግጣለሁ::

ይግባኝ ባይ

ቀን ---------------------------

**ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**
**አስተዳደር ፍ/ቤት**

ጉዳዩ:- <u>የመዝገብ ግልባጭ ስለመጠየቅ</u>

በይግባኝ ባይ አቶ / ወ/ሮ ---------------------------------------------- እና በመልስ ሰጭ ---------------------------------------- መካከል ሲካሄድ የነበረው የስራ ክርክር ------------------------ ቀን --------------- ዓ.ም የአስተዳደር ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጥቷል:: በመሆኑም ፍ/ቤ በሠጠው ውሳኔ ቅር ስለተሰኘሁ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት እንድችል የመዝገብ ግልባጭ እንዲሰጠን በትህትና እጠይቃለሁ::

ከሠላምታ ጋር

የአመልካች ስምና ፊርማ ---------------------------------

ቀን -------------------------------

**ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ**
**<u>አስተዳደር ፍ/ቤት</u>**

**ጉዳዩ:- <u>የውሣኔ ግልባጭ ስለመጠየቅ</u>**

በይግባኝ ባይ አቶ/ወ/ሮ ----------------------------------------------- እና መልስ ሰጭ ---------------------------------------- መካከል ሲካሄድ የነበረው የሥራ ክርክር -------------------------- ቀን --------------- ዓ.መ የአስተዳደር ፍ/ቤት ውሣኔ ሰጥቷል:: በመሆኑም ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ ለማስረጃነት ተገልብጦ እንዲሰጠኝ በትህትና እጠይቃለሁ::

ከሰላምታ ጋር

የአመልካች ስምና ፊርማ ---------------------------------------

ቀን ---------------------

**ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**
**አስተዳደር ፍ/ቤት**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ጉዳዩ:- <u>ለአፈፃፀም እንዲመራ መጠየቅ</u>**

በይግባኝ ባይ አቶ/ወ/ሮ ---------------------------------------------------------- እና በመልስ ሰጭ ---------------------------------------------------------- መካከል ሲካሄድ የነበረው የሥራ ክርክር ---------------------- ቀን -------------- ዓ.ም የአስተዳደር ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጭቷል:: ሆኖም መልስ ሰጭ / የፍርድ ባለዕዳ / በውሳኔው መሠረት ስላልፈፀመልኝ በአዋጅ ቁ . 262/1994 አንቀጽ 73/2/ መሠረት አፈፃፀሙ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲመራልኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ::

ከሰላምታ ጋር

የአመልካች ስምና ፊርማ -----------------------------------

## ማጣቀሻ


1. "የመንግሥት ሠራተኞችና መሥሪያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የትግልና የግምባታ ታሪክ" በሚል ርዕስ በኮሚሽኑ ጥር 1976 ዓ.ም የተዘጋጀ ጽሑፍ፣
2. በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስኤንሲ በየ3 ወሩ ከሚታተም ሜሪት መጽሔት በሕግና አስተዳደር ዓምድ የአስተዳደር ፍ/ቤት በኢትዮጵያ በአቶ መስፍን ታፈሰ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቅምት--1990 ዓ.ም፣
3. የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 262/94